# ዓለም ዋሾ!



ሻማ፣ ጥዋፍ በርቶ
        ሲል ውልብ-ውልብ
ጨለማን አጥፍቶ
        ወይ ሲያምር፣ ሲደምቅ
ሕፃኑም ያን አይቶ
        ምን ይሆን እያለ
ልቡ ሲደነቅ
        ዓይኑ እየዋለለ
ሄዶ እየዳኸ
        ጣቶቹን ዘርግቶ…
እሳቱም ልብ-ልብ!
        እሪ ብሎ ጮኸ
ዓለም ዋሾ፣ ዓለም አታላይ
                ዋይ! ዋይ!



ያማረ፣ የቀላ
        ጽጌ ረዳ አበባ
ሕፃኑም አየና
        መስሎት የሚበላ
በጣም ጐመጀና
        ዓይኖቹንም ከፍቶ
እጁንም ዘረጋው
        ቀርቦ፣ ተጠግቶ
ወደ ፊቱ ሳበው
        አበባውን ያዘና
ጨበጥ አደረገው
        እንደ ጡት ሊጠባ
ግን ዕሾኽ ሲወጋው…
        እሪ ብሎ ጮኸ
ዓለም ዋሾ፣ ዓለም አታላይ
                ዋይ! ዋይ!



ገ/ኢ. ጐርፉ።